# ብርቱካን ሚደቅሳ - የኛዋ ኦንግ ሳን ሱ ኪ (Aung San Suu Kyi.)



ኦንግ ሳን ሱ ኪ

ከወንድሙ መኰንን



ብርቱካን ሚደቅሳ

ነገር ከሥሩ፣ ውሀ ከጥሩ ይባላል። በርማ፣ በደቡብ ምሥራቅ ኤሲያ የምትገኝ አገር ናት። በደንቡ መጠሪት የነበረባት የተባብሩት ማያንማር (Union of Myanmar) ሲሆን አብዛኞቹ የዓለም መንግሥታት በተለምዶ “በርማ” ይሏታል። በርማ በፈረጀቹ አቆጣጠር 1962 ዓ ም ጀምራ በወታደር አገዛዝ ሥር ወድቃ ትገኛለች። የወታደሩ አምባገነን ደርግ የዓለምን ሕዝብ አስተያየት ትንሽ በርዞ ለብ ለማድረግ በ1990 ዓ ም ለይስሙላ ብሔራዊ ምርጫ ፈቅዶ ነበር። በነሱ አስተሳሰብ ተቃዋሚዎቹን ጨፍጭፈው ጸጥ ያደረጉና ሁሉንም የተቆጣጠሩት ስለመሰላቸው ተዘናግተው (አምባገነኖች መዘናጋት ልማዳቸው ነው) ምርጫውን አሸንፈው በየቀኑ የሚያላዝነውን የዓለም አቀፍ የሰብሰዊ መብት ተሟጋቾችን ላንቃ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመዝጋት ትንሽ ለቀቅ አድርገው ነበር። ዳሩ ግን ብሔራዊ ዲሞክራቲክ ሊግ (National League for Democracy — NLD) የተባለው የተቃዋሚ ፖሊቲካ ድርጅት ሳያስቡት ከዳር እስከዳር አንድም መቀመጫ ለጁንታው ሳያስቀር ጠቀለለው። አምባ ገነኖቹ ከእንቅልፋቸው ነቁ፥፤ ጉድ ፈላባቸው። ስልጣን ላለመልቀቅ የነበራቸው መንገድ አንድና አንድ ብቻ ነበር። እሱም የዲሞክራሲ ለምድ ደርበው ለማታለለ የሞከሩትን አውልቀው በዕውነተኛው ገጸ-ባሕይርያቸው፣ ግድያንና እሥራቱን ማጧጧፍ። የገደሉትን ገደሉ። ያሠሩትን አሠሩ። ያሰደዱትን አሳደዱ። ለዚህም ሥራ ከ1992 ጀምሮ ለነበሰ ገዳዩ የጁንታ መሪ ታን ሽው (Than Shwe) ስልጣኑን እንዲፈልገ እንፏልልበት በሰፊው ለቀቁት።

የበርማውን አምባ ገነን ገዥ በጦር መሣሪያ ለመዋጋት ብረሀ የገቡ አሉ። እየገደሉ ይሞታሉ። በሰላሙ መንገድ የተፋለሙት ከተራው ሕዝብ እስክ ቡዲስት ቀሳውስት በየቀኑ እየተሰው የገኛሉ። **ከዚያ ሁሉ ታጋዮች መሀል ግን፣ አንዲት ሴት የነጻነት የሰላም ታጋይ ከሁሉ ደምቃ እንደኮከብ የምታበራው ኦንግ ሳን ሱ ኪ ናት።** ኦንግ ሳን ሱ ኪ በጣም የተማረች፣ የደስ ደስ ያላት ሁሉም በጇ ሁሉም በደጇ ሊሆንላት የሚችል ምንም ያልጎደላት ምሑር ነበረች። ዳሩ ግን፣ ከጨካኙ ጁንታ ከሚሰጣት ሥልጣንና ከበሬታ ይልቅ፣ በጁንታው (ወይም የወታደሩ አምባገነን ደርግ) የታፈነውን ነጻነት ነጻ ልታወጣ ለሕዝቧ ስትል እራሷን ሰወታ ታሥራ ትገኛለች። የሚገርመው ይኽ ሁሉ እንግልት ሲደርስባት፣ አንዲት ቀን እንኳን ቢሆን ኦንግ ሳን ሱ ኪ ሰለራሷ ነጻነት ተናግራ አታውቅም። መታሥሯን መንገላታቷን ከመጤፍ የምትቆጥረውም አትመስልም። ከዘብጥያዋ ትንሽዬ ክፍል ሁና የምትጠይቀውና የምትናገረው ስልተራው የበርማ ሕዝብ ነጻነት ነው። ዓለምን ያሰደነቀችው ኦንግ ሳን ሱ ኪ፣ በእሥራት ላይ እያለች የ1991 ዓ. ም ኖቤል የሰላም ሎሪየት ሁናለች። የብዙ የዓለም የሰላም ታጋዮች ኮከብ ሁና ድምቃ ታበራለች። ታጋይዋ እየታገለች አሁንም ታታግላለች።

ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካ የምትገኝ አገራችን ስትሆን እሷም እንዲሁ በፈንጆቹ አቆጣጠር ከ1991 (፲፱፻፹፫) ዓ ም ጀምራ ከበርማ በባሰ በጨካኝ ቅጥረኛ አገዛዝ ሥር ወድቃ የነጻነት ብርሀን ጨልሞባት ሕዝቧ ግፉን በመግፋት ላይ ይገኛል። የኛዎቹ ከበርሞቹ የሚልዩብት ዋናው ነገር፣ ከጨካኝነትና ከአምባገነንነት አልፈው ተርፈው፣ ብሔራዊ ክሕደት የፈጸሙ የውጪ ጠላት ቅጥረኞች መሆናቸው ነው። ኢትዮጵያዊ ላልሆነ ሰው ይኸ ግራ የሚያጋባ ቢሆንም፣ ኢትዮጵያውያን ከሊቅ እስከ ደቂቅ ብሔራዊ አዋራጆቻቸውን ጠንቅቀው ያውቁአቸዋል። እነዚህ የአገር ክሕደት የፈጸሙ ወንጀለኞች፣ ሕዝቡን በዘር በመከፋፈል ልክ እንደ ቅኝ ገዢዎች ለይተውን መግዛት ሞክረዋል። ከዚያም አልፈው ተርፈው፣ አንዷን የአገራችንን ክፍል እንድትገነጥል በተባበሩት መንግስታትና በአፍርካ አንድነት ድርጅት ጽሕፈት ቤት ኮሪዶሮች ላይ ዶሴ ተሸክመው ተገንጣይዋን ክፍለ ግዛት እንድያውቁላት ተማልደው ዓለምን

ጉድ አሰኝተዋል። ያን ያሕል ክሕደትም በመፈጸማቸው ወደብ አልባ ዝግ አገር አድርገው እያፈራረሷት ይገኛሉ። ወንጃላቸው በዚህ ብቻ አልታቀበም። በታሪካችን ለመጀመሪያ ጊዜ ራሳቸውን ለሶስተኛ አገር በቅጥር በማቅረብ፤ የጎረቤት አገር ድንበርም ጥሰው ገብተው ሰላማዊቷን አገራችንን "ወራሪ" አስመስለዋታል። በሺዎች የሚቆጠሩ ይኽንኑ ጨካኝና ቅጥረኛ አምባ ገነን ሲታገሉ ሕይወታቸውን አጥተዋል። በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ዘብጥያ ወርደው ወህኒ ማቀዋል፣ እየማቀቁም ይገኛሉ። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ተሰደዋል።

የገደለውን ገድሎ፣ ያፈነውን አፍኖ፣ ያሰረውን አሥሮ፣ ያሳደደውን አሳድዶ አገሪቱን ሙሉ በሙሉ የተቆጣጠረ ስለመሰለው የኛው ቅጥር ነፍሰ-ገዳይ፣ የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾችን አሪታ ሊያፍን እሱም እንደ የበርማው ጁንታ፣ በፈረንጆቹ አቆጣጠር 2005 (በኛ አቆጣጠር ፲፱፻፺፯) ዓ ም "ለስሟ ቁና ሰፋች" እንዲሉ ብሐራዊ ምርጫ አውጆ ነበር። ኢትዮጵያውያንም የተገኘችውን ቀዳዳ ተጠቅመው፣ ቅንጅት ላንድነትና ለዲሞክራሲ (ቅንጅት) እንዲሁም የኢትዮጵያ ዲሞክራያውያን ሕብረት (ሕብረት) ጥላ ሥር በአጭር ጊዜ ውስጥ በመደራጀት ምርጫውን ከዳር እስከዳር በማሸነፍ ቅጥረኛውን ወያኔ ዛፍ ያጣ ጉሬዛ አስመሰሉት። የተደናገጠው መለስ ዜናዊ የተተኮሰባት ድኵላ ይመስል ሲደናበር የውሸት ዲሞክራሲ ካባውን ጥሎ፣ የነፍሰ-ገዳይ ዕውነተኛ ገጹን ተላበሰ። በዚህን ጊዜ ነበር ቅጥረኞቹ የሞት የሽረት የጥፋት መርባቸውን ልክ እንደ የበርማው አቻቸው የዘረጉት። የግድያ፣ የእሥራቱንና የማሳደዱን ተግባር አጧጡፈው፣ በጠራራው ጸሐይ፣ የዓለም ሕብረተሰብ እያያቸው ንጽሕ ደም አፈሰሱ። ከግድያም አልፈው፣ ተርፈው የቅንጅትን አመራር በጅምላው አሳደው በንቂስ ወህኒ አጎሩ። ለሆዱ ያደረውን ቦዘኔ ሰብስበው "ዳኛ" ብለውት እነሱው አገር የካዱት ቅጥርኛ ነብሰ ገዳዮች ብሶባቸው አገር ወዳዶችን በአገር ክህደት ወንጀል ከሰው እድሜ ልክ እሥራት አስፈረዱባቸው። በኋላ ላይ፣ ለምስመሰል "በምሕረት ፈታናቸው" በማለት "ይቅር ባይ አምላክ ነን" አሉ። ታዲያ ከታጋዮቹ መሀል እንዲሁ እንደ ኦንግ ሳን ሱ ኪ የፈነጠቀች ብርቱካን የምትባል የንጋት ኮከብ ድምቃ በራች።

ብርቱካን ልክ እንድ ኦንግ ሳን ሱ ኪ የተማረች፣ በሕግ ሙያ የተካነች፣ ሁሉም በጇ ሁሉም በደጇ ሊሆንላት የሚችል፣ የደስደስ ያላት ምንም ያልጎደላት ኢትዮጵያዊት ነበረች። በሙያዋ ትምሕርት እሷ ተፈትና ያለፈችው የሕግ የበላይነትን ነው። ዳኛም ሆና ስትሾም፣ ያመነችው ሕዝባችን የሕግ ከለላ ከተሰጠው መብቱ ተጠብቆለት ሠርቶ መግባት እንደሚችል ነበር። ዳሩ ግን፣ ገና ከጠዋቱ በ2001 (በኛ ፲፱፻፺፫) ዓ ም ነበር ተምራ በቲዎሪ ተፈትና ያለፈችውና የተግባር ፈተናዋ የተለያየባት። የጠላት ቅጥረኛው የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሥቃይ መለስ ዜናዊ፣ ኤርትራ የምትባለውን የቀድሞ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ግዛትን ከጠርነት ውርደት ከኢትዮጳይ ተዋጊዎች ከታደጋት በኋላ በአገር ክሕደት ወንጀል ከሰውት መቅመቅ ሊክቱት የተነሱትን የትግራይ ተቀናቃኞች ከነሥዬ አብረሀ ቡድን ለመትረፍ፣ የሕግ ዱላ ሊጠቀም ሞከረ። ዳሩ ግን ወጣቷ ዳኛ የአንገት አጥንት ሆነችበት። በውሸት የተከሰሰውን ሥዬ አብርሀን የሕጉን አንቀጽ ተጠቅማ በዋስ አሰናበተችው። ዓይን አውጣው ቅጥረኛ መለስ ዜናዊ ሲልኩት "ወዬት?" ባዩን "የይምሰል" ፓርላማ ሰብስቦ በአንዲት ጅንበር የሕጉን አንቀጽ አስለውጦ ሥዬን ስድስት ዓመታት በግፍ ወህኒ ቤት አጉሮ ዘጋበት። ወጣትዋ ዳኛ ይኽኔ ነበር በትክክል በሙያዋ መሥራት እንደማይቻላት የተረዳቸው። ሕግን ሥራ ላይ ማዋል የሚቻለው ሕግን እራሱን ነጻ አውጥቶ የበላይነቱን ማረጋገጥ ሲቻል ብቻ ነው ብላ ቆርጣ ተነሳች። ምርጫ ፺፯ የትግል አድማሷን አስፋላት። አቅጥጫዋን ሙሉ በሙሉ ነደፈላት። በቆራጥነቷ የቅንጀት አመራር ውስጥ ምክትል ፕሬዝደንት ሆነች። ወያኔ ሲያሳድዳትም፣ አናስነካትም ያሉ የፈረንሳይ ለጋሲዮን ዷሪዎች ሕይወታቸውን ሰውላት። የበለጠ ላለማስፈጀት እጇን ሰጥታ ወህኒ ወረደች። ከለሎቹ ከቅንጅት አመራር ጓዶቿ ጋር ታሥራ ማቀቀች። ቅንጅት ሲፈርስና አንድነት ለፍትሕና ለዲሞክራሲ ፓርቲ (አንድነት) ሲመሠረት ጀግናይቱ የመጀመሪያዋ፣ ለዚያውም ወጣት፣ ለዚያውም ሴት ፕረዝደንት ሆና ተመረጠች።

ብርቱካን ሥነ-ሥርዓት ያላት፣ ሰው አክባሪ ግን ካመነችው ንቅንቅ የማትል ቆራጥ ልጂት ናት። በቀላሉ ከሰው ጋር መግባባት የምትችል፣ ጨርሶ አጉል መኩራራት የማይታይባት፣ አንገቷን የደፋች፣ የማዳመጥ ችሎታዋ አስገራሚ የሆነች የወደፊት ብሩህ የኢትዮጵያ ተስፋ ናት። ብርቱካን፣ ሎንዶንን በቅርቡ ስትጎበኝ በብዛት ስለሕግ የበላይነት ስትናገር ትዕግስታቸው አልቆ ከተጋፈጡአት አድማጩችዋ አንዱ ይኸ ጸሐፊ ነበር። "እናንት (የአንንድነት አባላት)

ወያኔ ለማያከብረው ሕጉ ምን ገዶአችሁ ነው የምታከብሩለት” ስትባል፣ በሚጣፈጠው ለስለስ ባለው አንደበቷ፣ አንገቷን ሰብራ፤ “ሁሉም የሕግ የበላይነትን ካላከበረ፣ ሁሉም እንዳሻው ሕጉን ከጣሰው፣ የሕግ የበላይነት እንዴት ይከበራል? እኛስ ሕጉን አናከብርም ካልን፣ ከኢሕአዴግ በምን ተሻልን?” አለች። ለሕግ የበላይነት ስትከራከር የሚደርስባትን ለመቀበል፣ ዝግጁ ነበርች። ሕግን ከታሠረበት ነጻ ልታወጣ፣ እሷ ልትታሠር፣ ከገፋም ልትገደል ቆርጣ መነሳቷን ስትናገር ምንም ዓይነት ፍርሀት አልተየባትም። ከልቧ መሆኑንም የሚይስጠረጥር ምልክት ዓይኖችዋ ውስጥ አልተነበቡም።

የኛዋ ኦንግ ሳን ሱ ኪ፣ ብርቱካናችን ሰኞ ታኅሣሥ ፳ ቀን 2ሺ1 ዓመተ ምሕረት የወያኔ አፋኝ ቡድኖች በአራት መኪና ከበዋት አሥር ሁነው እጅና እግሯን ጠፍረው ተረባርበውባት ያዙአት። አዛውንቱ ፕሮፌሰር መስፍንም አብረዋት ነበሩ። “ለአንዲት ወጣት ሴት ይኸ ሁሉ ጋጋታ ምንድነው። በአንዲት ብጣሽ ወረቀት ነይ ብትሉአት፣ ሕግ አክባሪ በመሆኗ በቀጥታ እኮ ተመጣላችሁ ነበር” ብለው የአባትነት ምክር ሊሰጡ ሲሞክሩ ጋጠ-ወጦቹ የወያኔ ነፍሰ ገዳዮች “ምን አገባህ”፣ እያሉ ጸያፍ ስድቦችን አወርዱባቸው። በጠመንጃ ሰደፍ ቀጠቀጡአቸው። በእርግጫ የሮጀቱን ሽማግሌ አጣደፉአቸው። ይኸ ኢትዮጵያዊ ሥነ ምግባር የጎደለው ተራ ወሮብላነት ነው። ከዚያ በኋላ ብርቱካንን፣ የሕግ፣ የዲሞክራሲና የእኩልነት ሰማዕቷን እህታችንን፣ እንደማይሆን አድርገው፣ ጠልፈዋት አፍነዋት፣ ከሕግ ውጪ እያዳፉአት ወስደዋታል።

አባቶች ሲተርቱ፣ “የማይነጋ መስሏት … “ ይላሉ። የውጭ ጠላት ቅጥረኛው ወያኔ፣ ዛሬ ብርቱካንን አፍኖ ዕድሜ ይፍታሽ ብሎ ተባይ በወረሳት ወህኒ ቤት ወርውሮአታል። ዕድሜ ልኩን ኢትዮጵያን የሚገዛት መስሎት ነው። እነዚህ አገር ከሀዲ አምባገነኖች የሚያስገርሙት ነገር ቢኖር፣ ከቀደሙት አምባገነን ገዢዎች ታሪክ ትምሕርት ለመወሰዲ የሚችል ሒሊና የሌላቸው መሆኑ ነው። በአፋኞች እጅ ተይዞ የቀረ ሕብረተሰብ እስካሁን የለም። ይዋል የድር እንጂ አፋኞች፣ ጨቋኞች፣ በደለኞች ዕድሜ-ልክ አይገዟትም። እድሜ ልክም ስለማይገዙ፣ እድሜ ልክ የፈርዱባት እድሜ ልክ ታሥራ አትቀርም።፤ ይቆያል እንጂ እያንዳንዱ የእጁን ያገኛታል። እንኳን ከደደቢት ጫካ የፈለቁ ጋጠ-ወጦች፣ በመሣሪያውና በወታደሩ ወደር ያልነበረው ናዚም ከነመሪው ሂትለር መጨረሻው የመረረ ነበር። ኢንኳን የደደቢቱ ደደብ ዘረኛ፣ ይቅርና፣ ንኩሌር መሣሪያ የጨበጡ የራሺያ አምባገነኖች ሥርዓትም ተንኮታኩቶ ወድቋል። በትንሹ በእኛም አህጉር፣ እንደ ዩጋንዳው መሪ ኢዲ አሚንና የኢትዮጵያው የወታደር አምባገነን መሪ የመንግሥቱ መጨረሻ አያምሬ መሆኑን ማየት እንዴት እንዳቃታቸው ሲታሰብ ግርም ይላል። ያዙን ልቀቁን ይሉ የነበሩ የደርግ ባለሥልጣናት ዛሬ የት ናቸው? የወያኔም መሪዎች ተራቸውን ጠብቀው ይገቡአታል። የነሱ ይብሳል። ተራቸው ሲመጣ የእንሱም ደጋፊዎች “ድብቁን-ድብቁን” የሚሉበት ቀን ሩቅ አይሆንም። ያኔ ሁሉም ካድሬ “እኔ እኮ ምንም አላደርግኩም!” ይላል። አይተናላ! አዛውንቱን መርገጡን አሌ ማለቱ አያቀርም። ብርቱካን በሕይወቷ ካለች፣ ሕዝቧ “እልል!” እያለ ይቀበላታል። ሲሆን በሰላም፣ ካልሆነ በጉልበቱ ብርቱካንን ካፈኑበት ገብቶ ያስልቅቃታል። ብርቱካን ገና ትከበራለች። የነመለስ ጅምበር እየጥለቀት ሲትሄድ የነብርቱካን ጅምበር ወገግ ብላ ታበራለች።

ወያኔ መቼም ከደቡብ አፍርካው የአፓርታይድ ሥርዓት የከፋ የጭካኔ መጨረሻ የሆነ አገዛዝ ነው። ምናልባት ይማር እንደሆነ ለራሱ ሲል ከመሰሎቹ ከቀድሞ የአፓርትይድ ሥርዓት አካሂይጆች ጋር ቢመካከር ይበጀዋል። አፓርታይድ ለራሱ ሲል ሕዝቡን ይቅርታ ጠይቆ፣ ለ27 ዓመታት ያሰረውን ማንዴላን ፈትቶት አባሎቹን ከእልቂት አትርፏል። ወያኔ ከደደቢት በረሀ በመወጣቱ ደደብ ሁኖ መማር ካላቃተው በስተቀር ከነሱ ልምድ በወሰደ። ጨው ሆይ! ለራስህ ስትል ጣፍጥ!